ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ
Kinijit for Unity and Democracy North America Support Committee
1629 K Street, NW Suite 300 ■ Washington, DC, 20006 ■ web: www.ksa-america.org
Tel: (202) 565-7864 ■ Fax: (202) 331-3759 ■ e-mail: kinijitusa@ksa-america.org

10/04/2008

# መግለጫ

የመኢዐድ/ቅንጅት የአሜሪካ ድጋፍ ሰጭ ማኅበር በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.1.2. መሠረት ዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባውን ከኦክቶበር 3–4 2008 ድረስ ለሁለት ተከታታይ ቀኖች በቴሌ ኮንፍረንስ አካሂዷል።

ስብሰባው በቴሌ ኮንፍረንስ የተደረገበት መሠረታዊ ምክንያትም፡ የማኅበሩ መማክርት ም/ቤት ከቻፕተር አመራሮች ጋር በ9/4/08 ባካሄዱት የቴሌ ኮንፈረንስ፣ በአካል ተገናኝቶ ዓመታዊ ስብሰባውን ማካሄዱ ተገቢና ሕጋዊ መሆኑን አጢኖ፣ ነገር ግን የሚያስከትለው የትራንስፖርት፣ የሆቴልና የምግብ ወጭ ከፍተኛ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ለዚህ ተብሎ የሚወጣው ወጭ አገር ቤት ለሚካሄደው ትግል ቢውል ሊጠቅም እንደሚችል በማመን ስብሰባው በቴሌ ኮንፍረንስ ሆኖ፣ ስብሰባው በአካል ቢደረግ የሚያስከትለው ወጭ በአማካኝ ተሰልቶ፣ በቻፕተር ደረጃ የተወሰነ ተዋጥቶ ለአገር ቤት ገቢ እንዲደረግ በተወሰነው ውሳኔ መሠረት የተደረገ መሆኑን ስብሰባው ተገንዝቧል።

ይህ የማኅበሩ 6ኛ መደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ ከፍ ሲል በተጠቀሰው መሠረተ ሃሳብ መሠረት ቀደም ሲል በተያዘለት የጊዜ ሰንጠረዥ፣ የአስራ አራት ቻፕተሮች ተወካዮችና የማህበሩ መማክርት ም/ቤት፣ የስነ ምግባርና የኦዲት ኮሚቴ አባሎች በተገኙበት ዓመታዊ ስብሰባውን በተሳካ ሁኔታ አካሂዷል።

ስብሰባው በተሳታፊዎቹ በሙሉ ድምጽ በፀደቁ 6 አጀንዳዎች ሰፊና ጥልቅ ውይይት በማካሄድ ጠቃሚ ውሳኔዎችን አሳልፏል።

በዚህም መሠረት

1ኛ በመማክርት ም/ቤቱና በስነ-ምግባር ኮሚቴ የቀረቡትን ሪፖርቶች አዳምጦ ከገመገመ በኋላ ሪፖርቱን በመቀበል፣ የሚቀጥለውን ዓመት የሥራ ዕቅድና በጀት አጽድቋል።

2ኛ የማኅበሩ 5ኛ ጠቅላላ ስብሰባ በሰጠው ውሳኔ መሠረት፣ ተሻሽሎና ተስተካክሎ በመማክርት ም/ቤቱ በፀደቀው መተዳደሪያ ደንብ ላይ፣ ማለትም፡ አንቀጽ 5.3.6 እና 6.2.13 ላይ የስብሰባው ተሳታፊዎች ባቀረቡት የማሻሻያ ሀሳብ፡ አመርቂ ውይይት